# ነፍሰ ጡር ሰራተኞች እና አዲስ ወላጆች

## በሥራ ላይ እርግዝና

ነፍሰ ጡር ከሆኑ፣ የመጠየቅ መብት አሎት እና አሰሪዎ የሚከተሉትን ማቅረብ ይኖርበታል፡-

- በጣም በተደጋጋሚ ወይም ረዘም ያለ መጸዳጃ ቤት፣ የምግብ እና የውሃ እረፍቶች፤
- መቀመጥ፤ እና
- ከ20 ፓውንድ በላይ የማንሳት ላይ ገደብ።

ከጤና እንክብካቤ አቅራቢ ወይም ከዳዉላ ምክር ሲሰጥዎ ሌሎች የስራ ቦታ ለውጦችን የመጠየቅ መብት አልዎት። ነፍሰ ጡር ስለሆኑ ቀጣሪዎ የስራ ሁኔታዎን እንዲያስተካክሉ ሊጠይቅዎት አይችልም።

## እርግዝና እና የወላጅ የእረፍት ፍቃድ ከስራ ቦታ

በእርግዝና ወቅት ወይም ልጃቸውን ሲወለዱ ወይም በጉዲፈቻ ወቅት ሰራተኞች እስከ 12 ሳምንታት ያለክፍያ ፈቃድ ሊጠይቁ እና ሊወስዱ ይችላሉ። ሰራተኞቻቸው የአሰሪያቸው መጠን ወይም ለቀጣሪያቸው የሰሩበት ጊዜ ምንም ይሁን ምን ለዚህ ፈቃድ ብቁ ናቸው።

የእርግዝና እና የወላጅነት ፈቃድ ለሚከተሉት ሊወሰድ ይችላል፡-

- ለቅድመ ወሊድ እንክብካቤ፤
- በእርግዝና ወይም በተዛማጅ የጤና ሁኔታዎች ምክንያት አቅም ማጣት፤
- ልጅ መውለድ ወይም ጉዲፈቻ፤ ወይም
- ልጅ ከተወለደ ወይም ከጉዲፈቻ በኋላ በወለደ ወይም ባልወለደ ወላጅ የግንኙነት ጊዜ።

ቀጣሪዎች በወሊድ ወይም በጉዲፈቻ በ12 ወራት ጊዜ ውስጥ የእረፍት ፍቃድ ጥያቄ መቼ ሊቀርብ እንደሚገባ እና የእረፍት ፍቃዱ መቼ መወሰድ እንዳለበት ምክንያታዊ ፖሊሲዎችን ማዘጋጀት ይችላሉ።

በእርግዝና ወቅት ከታመሙ ወይም ከወሊድ በኋላ ለማገገም ጊዜ ካስፈለገዎት፤ በአሰሪ የሚሰጡ ጥቅማ ጥቅሞችን ለምሳሌ የሕመም ፈቃድ ወይም የአካል ጉዳት ፈቃድ መጠቀም ይችላሉ።



የሚኒሶታ የሚከፈልበት የቤተሰብ እና የህክምና እረፍት ፈቃድ ህግ፣ በእርግዝና ወቅት ወይም በኋላ የሚከፈልበት የእረፍት ፈቃድ የሚሰጥ ህግ ሲሆን፣ ከጃንዋሪ 1፣ 2026 ጀምሮ ተግባራዊ ይሆናል።

## በሥራ ቦታ ወተትን ማለብ

በስራ ቦታ ወተትን ለማለብ ከወሰኑ አሰሪዎ መጠኑ ምንም ይሁን ምን የሚከተሉትን ማቅረብ አለበት፡-

- ማካካሻ ሳያጡ ወተትን ለማለብ የእረፍት ጊዜያትን መስጠት፤ እና
- ወተትን ለማለብ ንጹህ፣ ግላዊ እና ደህንነቱ የተጠበቀ ቦታ፡-
  - መጸዳጃ ቤት ያልሆነ፤
  - ከእይታ የተከለለ፤
  - ከስራ ባልደረቦች እና ከህዝብ ጣልቃ ገብነት የጸዳ፤
  - ለሥራ ቦታው ቅርበት ያለው፤ እና
  - የኤሌትሪክ ሶኬት መዳረሻ ያለው።

ለዚህ መስፈርት ጥቂት ልዩ ሁኔታዎች ሊኖሩ ይችላሉ።.

በፍላጎትዎ መሰረት ወተት መቼ እንደሚያልቡ መምረጥ ይችላሉ፤ ይህም ማለት በተለመደው የሚከፈልበት እረፍት ጊዜ፣ በተለመደው ያለክፍያ እረፍት ጊዜ ለምሳሌ እንደ የምግብ እረፍት ወይም በሌላ ጊዜ ውስጥ ወተት ማለብ ማለት ነው።

በሥራ ቦታ ወተትን ለማለብ የእረፍት ፈቃድ፣ ለእርግዝና ማረፊያ ወይም ለዕረፍት በመጠየቅዎ ወይም በመውሰድዎ፣ አሰሪዎ በእርስዎ ላይ በቀል ወይም አሉታዊ እርምጃን መውሰድ ህግን የሚቃረን ነው።

## ያነጋግሩን

የሰራተኛ ደረጃዎችን በ 651-284-5075 ወይም dli.laborstandards@state.mn.us.


DEPARTMENT OF LABOR AND INDUSTRY
Labor Standards • 443 Lafayette Road N. • St. Paul, MN 55155
651-284-5075 • 800-342-5354 • dli.mn.gov • dli.laborstandards@state.mn.us


ማሳሰቢያ፡ ይህ የሚኒሶታ ህግ አጭር ማጠቃለያ ነው። እንደ መመሪያ የታሰበ ነው እና ተዛማጅ ለሆኑ የሚኒሶታ ሕጎች እንደ ምትክ ተደርጎ ሊወሰድ አይችልም።

Version 0623